# የስቴት ዲፓርትመንት የክስ ሪፖርት

# “ሳይገሉ ጐፈሬ ሳያጣሩ ወሬ”

ከእንዳለ መብራቱ 6/13/12

ሰሞኑን የአሜሪካ መንግስት /State department of America/ በኢትዮጵያ ያለውን የሰብአዊ መብት አያያዝን አስመልክቶ መግለጫ አውጥቶ ነበር፡፡

የወጣውን መግለጫ በወፍ በረርም ቢሆን ለመቃኘት እንደሞከርኩት በአብዛኛው የዓመቱ ሪፖርት ያልተካተተበት ከመሆኑም በላይ ሪፖርቱን ለማሟላት ሲባል በ2002 ዓ.ም እና ከዛ በፊት "ተፈጸሙ" ያላቸውን የሰብአዊ መብት ጥሰቶች አጭቆ ያቀረበበት ነው፡፡

ለዘረዘራቸው "የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች" በምንጭነት የተጠቀሱት ግንቦት 7፣ ኦነግ፣ ኦብነግ፣ መድረክ፣ ኦብኮን እና ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶችን እንዲሁም "የፖለቲካ ታሳሪዎችን" ሲሆን፤ ከነዚህ በተጨማሪ የሰብአዊ መብቶች ዐቃቤ /HRW/ እና አምነስቲ ኢንተርናሽናልም ይገኙበታል፡፡ በመንግሥት ወኪሎች ተፈፀሙ የተባሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ክሶች የቀረቡት በአብዛኛው ከኦብነግ ምንጮች እንደሆነ የሚያትተው ሪፖርቱ፤ ይህም በዲያስፖራ ጦመሮች (Blogs) በኩል እንደሆነ እና መረጃው በትክክል ሊጣራ እንዳልቻለ ይገልፃል፡፡ ታዲያ መረጃው በትክክል ሊጣራ እንዳልቻለ እያስረዱ ለምን ለክስ መሮጥን ወደዱ? “ሳይገሉ ጐፈሬ ሳያጣሩ ወሬ” ማለት ይሄ ነው፡፡ ሌሎቹን መረጃዎች ደግሞ ታማኝ ምንጮች፣ የዐይን እማኞች፣ የታሳሪዎች ቤተሰቦች፣ ተቃዋሚዎች በሰጡት መረጃ እያሉ አድበስብሶ የመሄድ ነገር ይታይበታል፡፡

በክስ መልክ በተዘጋጀው "የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች" ውስጥ በ2002 ዓ.ም የተከናወነውን ምርጫ አስመልክቶም ተፈፀሙ ያላቸውን ድርጊቶች አቅርቧል፡፡ ከሪፖርቱ መረዳት የሚቻለው ግን በየጊዜው በሚያቀርቡት ሃሰተኛ ውንጀላዎች መሠረት የዘንድሮው የክስ ሪፖርት አልሟላ ስላላቸውና ክስ የሚያቀርቡበት እና ስም የሚያጠፉበት ነገር ስላጠራቸው ባለፉት ዓመታት ያቀረቡዋቸውን ሪፖርቶች በድጋሚ ሊያቀርቡ ተገደዋል፡፡

በክስ ሪፖርቱ ላይ ስለምርጫው ስለ"ፖለቲካ እስረኞች"፣ ስለ በጐ አድራጐት ማህበራት ስለጋዜጠኞች ባቀረቡት 40 ገጽ በሚደርስ ዘገባቸው በተለያዩ ገጾች ያንኑ ሃሳብ ደጋግመው አቅርበዋል፡፡

በሪፖርታቸው ከ100 በላይ "የፖለቲካ እስረኞች" ማለትም የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት፣ ጋዜጠኞች እና ጦማሪዎች / Bloggers / በመንግሥት መያዛቸውን፣ ከነዚህም መካከል 14ቱ በፀረ ሽብር አዋጁ

መያዛቸውን ጠቅሰዋል፡፡ ሆኖም በሌላ ገጽ የፖለቲካ እስረኞችን አስመልክቶ ባቀረቡት ሪፖርት ደግሞ፤ የአገር ውስጥና የዓለምአቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን /መያዶችን/ በማስረጃነት በመጥቀስ ከ200 - 300 የሚሆኑ የፖለቲካ እስረኞች እንደታሰሩ ገልፀዋል፡፡ ሪፖርቱ መንግሥት ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች እሥረኞችን እንዳይጐበኙ ገድቧል ብሎ ከፃፈ በኋላ በሌላ ገፅ ደግሞ ዓለም አቀፉ የቀይ መስቀል ማህበርና ሌሎች ዓለማቀፍ ድርጅቶች እሥረኞችን መጐብኘታቸው ጠቅሷል፡፡ ይህም የክስ ሪፖርቱ እርስ በርስ እንደሚጣረስ የሚያሳይ ነው፡፡

ከክሶቹ መካከል ደግሞ የሚገርመው በዕውቀት ማነስ፣ በድህነትና በጐጂ ባህላዊ ልምዶች በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈፀሙ ክስተቶችን በመንግሥትና በአስፈጻሚ አካላቱ እንደተፈጸሙ አድርጐ ማቅረቡ ነው፡፡ ከነዚህም መካከል በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጾታዊ ጥቃቶችና ማህበራዊ አድልዎ፣ በህፃናት ላይ የሚፈጸም ድብደባ፣ ህፃናትን ለኢኮኖሚያዊና ዝሙታዊ ብዝበዛ መጠቀም፣ የሴት ልጆች ግርዛት / female genital mutilation/ ጠለፋ፣ አስገድዶ መድፈር፣ ጾታ ተኮር የሰዎች መድልዎ፤ በኤች አይ.ቪ. ኤድስ የተያዙ ሰዎችን ማግለልና የሥራ መብቶቻቸውን መገደብ በኃይል ማሠራትና የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ የተጠቀሱት ናቸው፡፡

እነዚህ ከላይ በዝርዝር የተጠቀሱትና በክስ መልክ የቀረቡት ጉዳዮች በመንግሥት ምክንያት የተፈጸሙ እንዳልሆኑ ማንም ሰው የሚመሰክረው ሃቅ ነው፡፡  በኢትዮጵያ መንግሥት የፀጥታ ኃይል አባላት በፖሊስና በሚሊሺያዎች ተፈፀሙ የተባሉት እነዚህ ክሶች በተጨባጭ ማስረጃና ቁጥር ሳይሆን የክስ ሪፖርቱን ለማሟላት ያህል በዝርዝር የቀረቡ ናቸው፡፡

የተጠቀሱት ጉዳዮች አልተከናወኑም ለማለት ሳይሆን፣ የተከናወኑት የተማረ የሰው ኃይል እጥረት ባለባቸው ጐጂ ባህላዊ ልምዶች በበረከቱባቸው በገጠርና ጠረፋማ አካባቢዎች ነው፡፡ በዕውቀት ማነስ፣ በተማረ የሰው ኃይል እጥረት፣ በድህነትና፣ በጐጂ ባህላዊ ልምዶች መበራከት ምክንያት በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የተፈጸሙ ክስተቶችን መንግሥትና ገዢው ፓርቲ እንዳካሄዱት አድርጐ አንስቶ መለጠፍስ አሳማኝ ነው?

ይልቅ መንግሥት ከላይ የተጠቀሱት ጐጂ ባህላዊ ልምዶች ከየአካባቢው እንዲወገዱ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ ከሃይማኖት ተቋማት፤ ከፌዴራልና ክልል አስፈጻሚ ተቋማት ጋር በመሆን በሠፊው በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡ ጐጂ ባህላዊ ልምዶችም ከዓመት ዓመት በመቀነስ ላይ ናቸው፡፡

በጐጂ ባህላዊ ልምዶች መበራከት ምክንያት በየቦታው የሚከናወኑትን ክስተቶች መንግሥት በትምህርት፣ በሥልጠና ለማስወገድ እየጣረ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስወገድ እና ለመከላከል ከኢትዮጵያ ጐጂ ባህላዊ ምልዶች አስወጋጅ ኮሚቴ ከሌሎች የዕርዳታ ድርጅቶች፣ ከኦርቶዶክስ፣ ከእስልምናና ከካቶሊክ የሃይማኖት ተቋማት ጋር በመሆን ሠፊ ሥራ ተሠርቷል፤ በመሠራትም ላይ ይገኛል፡፡

ትምህርት የልማት መሠረት ብቻ ሳይሆን የሰብአዊ መብት ጉዳይም ነው፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥትም የሴቶችንና የሕፃናትን የትምህርት ዕድልና ተሳትፎ ለማስፋት፣ ሰብአዊ መብታቸውን ለማስጠበቅ የተለያዩ እርምጃዎችን ወስዷል፡፡ ሴት ተማሪዎች ያለባቸውን ማህበራዊ ጫና ጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት ከግምት በማስገባት በመንግሥት ልዩ ትኩረት ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት / ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች/ እንዲገቡ አዎንታዊ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመከላከልና ሂደቱንም ሕጋዊ ለማድረግ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከፖለቲካ አካላትና ከእርዳታ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ሠፊ ሥራ ተሰርቷል፡፡ ችግሩን ለማስወገድና ለዜጎች ግንዛቤ ለመስጠት በፖሊስና ኅብረተሰብ ቴሌቪዥን ሠፊ ፕሮግራሞች ለረጅም ጊዜ ተሠርቷል፡፡ በሌሎች መገናኛ ብዙሃንም ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ ይህም መንግሥት ችግሩን ለመቀነስና ለማስወገድ የሰጠውን ትኩረት ያሳያል፡፡

የበጐ አድራጐት እና ሲቪል ማኅበራትን አስመልክቶም ባቀረቡት ሪፖርት የበጐ አድራጐት እና ሲቪል ማኅበራት አዋጅ ከወጣ ወዲህ /2001 ዓ.ም/ አዋጁ በሲቪል ማኅበራትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እንቅስቃሴ ላይ ብዙ ገደቦችን በመጫኑ እንቅስቃሴያቸው በከፍተኛ ሁኔታ መቀነሱንና መዳከሙን አትተዋል፡፡

ሆኖም የተገለፀው የበጐ አድራጐት ድርጅቶች እና ማኅበራት አዋጅ ከወጣ በኋላ የዘርፉ የአገልግሎት አሠጣጥ መሻሻል ማሳየቱንና የአዳዲስ ተመዝጋቢ ማኅበራትና ድርጅቶች ቁጥር መጨመሩን የክርስቲያን ተራድኦና ልማት ድርጅት ሰሞኑን ባዘጋጀው ስብሰባ ላይ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አቶ ኃይማርያም ደሳለኝ ባደረጉት ንግግር ገልፀዋል፡፡ በዚህ ስብሰባ ላይ አሥር የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማኅበራት በዘርፉ መልካም ሥራ በማከናወንም ተሸልመዋል፡፡

ቀደም ሲል በየዓመቱ በአማካይ 76 ያህል የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ይመዘገቡ ነበር፡፡ አዋጁ ከወጣ በኋላ /ከ2001 ዓ.ም ወዲህ / ግን 332 የበጐ አድራጐት ድርጅቶች መመዝገባቸው ተገልጿል፡፡ ማኅበራቱ የሚሰጡት አገልግሎት የበለጠ ጥራት ያለው መሆኑም በግምገማ ተረጋግጧል፡፡ ባጠቃላይ አዋጁ የፈጠረላቸውን ምቹ ሁኔታ ተጠቅመው 1 ሺህ 43 አዳዲስ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማኅበራት ተመዝግበዋል፡፡ ይህ ደግሞ የአሜሪካ ስቴት ዲፓርትሜንት መያዶችን /NGO’s / መዳከምን አስመልክቶ ካቀረበው ሪፖርት በተቃራኒ የሚቀርብ ማስረጃ ነው፡፡

በሪፖርቱ ላይ የኦጋዴን ነፃ አውጪ ግንባር ታጣቂ አንድ የእርዳታ ሠራተኛ መግደሉንና ሌሎች ሁለት የሰብአዊ ዕርዳታ ሠራተኞችን ከስድስት ሳምንት በላይ በማገት ማቆየቱን ጠቅሷል፡፡

በርግጥ ሪፖርቱ በአብዛኛው ለይስሙላ ያህል እንደቀረበ ለመረዳት ቢቻልም፣ ቀደም ሲል ይቀርቡ ከነበሩት ሪፖርቶች በተሻለ አዎንታዊ ነገሮች ለመጥቀስ ሞክሯል፡፡ ከፖለቲካ ጋር በተያያዘ የተፈፀመ ግድያ በመንግሥትም ሆነ በወኪሎቹ አለመኖሩ ከፖለቲካ ጋር በተያያዘ የጠፉ ወይም የተሰወሩ ሰዎች አለመኖራቸውን ገልጿል፡፡

የክልል ባለሥልጣናት በመደበኛነት መያዶች ያለ ሦስተኛ ወገን ተሳትፎ ታራሚዎችን እንዲጐበኙ እንደሚፈቀድላቸው የጠቀሰ ሲሆን፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርሲቲያን እና በሌሎች ሃይማኖት ድርጅቶች አሸማጋይነት መንግሥት በዘር ማጥፋት ወንጀል ተከሰው የሞት ፍርድ የተፈረደባቸው 23 የደርግ ባለሥልጣናት ፍርድ ወደ ዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት እንደ ተቀነሰላቸውና 16 የደርግ ባለሥልጣናት ከእስር በይቅርታ እንደተፈቱ ያትታል፡፡ የግንቦት 7 አባል የሆኑት እና የዕድሜ ልክ እሥራት የተፈረደባቸው አቶ ጽጌ ሃብተማርያም የተባሉ እሥረኛም ከእሥር እንደተፈቱ ይገልፃል፡፡

በአገሪቱ የፍትህ መጓተት እንደሚታይ የሚገልፀው ሪፖርቱ ይህ የተከሰተው በአብዛኛው በረጅም የፍትህ ሂደቶች ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪም በእሥረኞች መብዛት፣ በፍትህ ባለሙያዎች አቅም ማነስ እና በባለሙያዎች እጥረት መሆኑን ጠቅሷል፡፡

መንግሥት ለፖሊስ፣ ለፀጥታ ኃይል አባላትና ለመከላከያ ተቀጣሪዎች የሰብዓዊ መብት ሥልጠና መስጠቱን እንደቀጠለ በዓመቱ ውስጥ መንግሥት ጀስቲስ ፎር ኦል ፕሪዝን ፌሎሽፕ ኢትዮጵያ የተባለ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ከኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ጋር በመተባበር የሰብአዊ መብት ስልጠናዎችን ለፖሊስ ኮሚሽነሮች፣ ለዳኞች፣ ለዐቃቤ ህግ ባለሙያዎች፣ ለማረሚያ ቤት አስተዳደሪዎችና ለሚሊሺያዎች /በትግራይ፣ ኦሮሚያ፣ አፋር፣ ደቡብ ክልል ፣ ለጋምቤላ እና ለአዲስ አበባ/ መስጠቱንም ከቀረበው ሪፖርት መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ይኸው መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት /JFA —PFE / ከመንግሥት ጋር በመተባበር የማረሚያ ቤቶችን ሁኔታ ለማሻሻል በጋራ እየሠራ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የፌዴራል ማረሚያ ቤቶችን ጨምሮ ብዙ የማረሚያ ቤቶችን ይዞታና ለታራሚዎች የሚሰጡ የተለያዩ አገልግሎቶችን ለማሻሻል ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡ በአዳማ እና በመቀሌም አርአያ /ሞዴል/ የሚሆኑ በተሻለ መልኩ ጠቃሚ ቁሳቁሶች የተሟሉላቸው ማረሚያ ቤቶች ተዘጋጅተዋል፡፡

ታዲያ እውነታው ይህ ሆኖ ሳለና የኢትዮጵያ መንግሥት የፀረ ሽብር አጋር ነው ብለው እያመኑ በሌላ በኩል ደግሞ መንግሥት የሰብአዊ መብት ጥሰት እንደሚፈጽም አስመስለው በሪፖርታቸው ባካተቱት ሃሰተኛ ክስ እንደ መረጃ ምንጭ የጠቀሷቸው ግን ኢትዮጵያ በፓርላማዋ በአሸባሪነት የፈረጀቻቸውን እንደኦብነግ እና ግንቦት ሰባት የመሳሰሉ አካላትን ነው፡፡

*ምንም እንኳን የቀረበው ሪፖርት የተአማኒነት እና የምንጭ ችግሮች ቢኖሩበትና ሚዛናዊነት ቢጐለውም ቀደም ሲል ይቀርቡ ከነበሩት ሪፖርቶችን በተወሰነ መልኩ በመንግሥት በኩል የተከናወኑ አንዳንድ አዎንታዊ ሥራዎችን ለማቅረብ ሞክሯል፡፡ በዚህ ረገድ ኢትዮጵያን አስመልክተው በቀጣይ የሚያወጧቸው ሪፖርቶች በተቻለ መጠን ትክክለኛውንና ተጨባጭ ሁኔታዎችን ከግንዛቤ ያስገቡና ታአማኒ እንዲሆኑ አሁንም ብዙ ርቀት መጓዝ ይኖርባቸዋል፡፡*